# ወዮልን!

በመጀመሪያው ቀን ሀ ብሎ ቢፈጥራት፣
ብዙ ተባዙባት ብሎም ቢባርካት፣
ቸር እንዳትመስላችሁ መሬት ቂመኛ ናት።

ሁሉን ቻይ ናት ብለን ምራቅ ብንተፋባት፣
እድፍ ብንደፋባት ሽንት ብንሸናባት፣
ታስጎነጨናለች ደፍቃ መቃብር  ውስጥ።

አታዬንም ብለን ግፍ ብንፈጽምባት፣
ሰውን ብናሰቃይ ብናስር ብንገልባት፣
ታግሳ ታግሳ የምትበቀል ናት፣
ሥጋን ቡን አድርጋ ከአፈር በመቀየጥ፣
አጥንትንም ጎርሳ መቅኔውን በመምጠጥ።

አለም በቃን ብለን የውሸት ቆብ ደፍተን፣
እንደ ሐዋርያ መስቀልን ጨብጠን፣
ጳጳስ ፓትርያርክ አቡንም ተብለን፣
የደጀ ሰላም በር ጥርቅም አርገን ዘግተን፣
አስራት ከፋይዎችን ቆመን አስፈጅተን፣
ለነፍሰ ገዳይዎች ጧት ማታ እየሰገድን፣
ደሞ እንደ መለኮት ሕዝብንም የከዳን፣
ወዮልን! ወዮልን! መሬት ስትጎርሰን፣
ከአስቆሮቱ ይሁዳ ከጳውሎስ ካልተማርን።

በክፋት በተንኮል በምዕራብ ተገፍተን፣
ወንበር ላይ የወጣን በደም ተጨማልቀን፣
አገር ለመተልተል የባእድ ካርታ ይዘን፣
የዘር ዕጸ-በለስ በሕዝብ በትነን፣
በቋንቋ መንጋጋ እርሰ በርስ እናከሰን፣
ወዮልን! ወዮልን! መሬት ስትውጠን፣
እንደ በርባን መለስ ንስሃ ሳያጥበን።

በአምሳሉ ፈጣሪን እግዚአብሔርን ትተን፣
ገዥን እምንለምን ጎብጠን ተንበርክከን፣
ሚኒስቴር ቆንሱላ ሥራ አስኪያጅ ተሹመን፣
ሁሌ እምንታዘዝ ሎሌ ባርያ ሆነን፣
ሕዝብን እያስለቀስን ደም እንባ እያስነባን፣
ወዮልን! ወዮልን! ለዚህ ክህደታችን፣
መሬት ላንቃ ከፍታ ጠቅልላ ስትውጠን።

ዲታ ጽድቅ አይወርስም ያለውን ረስተን፣
በስስት በጉጉት ወረርሽኝ ተለክፈን፣
ካድሬን ደጅ ጠንተን ጉቦንም ነስንሰን፣
በስንቱ ጉረሮ ስንጥቅ እንጨት ሰደን፣
ዶላሩን ዩሮውን ፓውንዱን እያጨቅን፣
ብንከብር ብንጠነባ ብንተፋ ወቢን፣
በአየር ላይ ብንከንፍ ምድር ተጠይፈን፣
የማታ ማታ ግን መሬት አትለቀን፣
እንደ አበጠ ፊኛ ሳታስተነፍሰን።

በስርቆት በጉቦ ንብረት አግበስብሰን፣
ጽድቅንም በመቅቡጥ ለመሸመት ቃቶን፣
ጉቦ በስለት መልክ ለታቦት ያስገባን፣
ወዮልን! ወዮልን! መቃብር ሲውጠን፣
ይህን መሰሪነት መሬት ስጠይቀን።

ከሕዝብ ገላ ላይ እንደ መዥገር በቅለን፣
ስጋውን እያኘክን ደሙንም እየማግን፣
ገንዘብ አግበስብሰን በንብረት ጠንብተን፣
ጉልበት ሸብረክ ሲል ሞት ከሩቅ ሲሸተን፣
ንስሐ ሳንገባ ሕዝብም ይቅር ሳይለን፣
ደብረ ሊባኖስ ውስጥ መቃብር የሰራን፣
ከገሃነብ እሳት የሚያድነን መስሎን፣
ወዮልን! ወዮልን! መሬት ስትውጠን።

ነገ ጧ ለሚለው ለከርሳችን ብለን፣
ህሊናን ማተብን እንደ ክር ቦጭቀን፣
ወንጀልን አርግዘን ቅርቀብም ተጭነን፣
እንደ እባብ እየተሳብን በምንዝ ላይ ያለን፣
ወዮልን! ወዮልን! አፈሩ ሲጫነን፣
ጉድጓድ ስንገባ በከፈን ተቋጥረን።

ዲግሪያችንን ካራ ሹካና ማንኪያ አርገን፣
ጨጓራ ስንሞላ ስንጠቀጥቅ የኖረን፣
ለመለኮት ሳይሆን ለካድሬ እየሰገድን፣
ለመስሎ አዳሪነት ለፍርሃት ገብረን፣
ምድር ላይ የሚቀር አሻራ የሌለን፣
ይዘነው እምንሄድ ስንቅ ያላዘጋጀን፣
ወዮልን!  ወዮልን! ይች አለም ስትበቃን፣
በሳጥን ሸክፈው ጉድጓድ ውስጥ ሲከቱን።

የስንቱን ሕዝብ እንባ እንደ ዶፍ አዝንበን፣
የአእላፍንም ደም እንደ ጎርፍ አውርደን፣
በሐጥያት ባህር ውስጥ እየዋኘን ያለን፣
ያቺ ሰዓት ስደርስ ወዮልን! ወዮልን!
መሬት አፏን ከፍታ ዋጥ ስታደርገን።

የሕይወት ታሪክ ንባብ ፍታት አያድነን፣
ሳጥንና ከፈን ጠበቃ አይቆሙልን፣
የመቃብር ሐውልት አያማልድልን፣
መሬት በውስዋ አርጋ ስትመረምረን፣
ስንቱን እንደፈጀን፣ ስንቱን እንዳስለቀስን፣
ስንቱን እንደዘረፍን፣ ስንቱን እንዳሰደድን፣
ስንቱን እንዳታለልን፣ ስንቱንም  እንደካድን፣
ምስጥን ቅጣት ሰጪ ዳኛ አርጋ ጉንዳንን።

የሰው ደም እንደ በግ ስናፈስ ኖረን፣
ጊዜው ስለሰጠ ስልጣኑ ስላለን፣

ቀኑን ሙሉ ፈተው ስላሴ ቢቀብሩን፣
ሲኦል ከመንጫረር ከመንደድ አንድን!

ከነፈስ ገዳይ ጋር እየተሞዳሞድን፣
የንጹሐንን ነፍስ በምድር ያስቃዪን፣
ሕዝቡ ማቅን ሲለብስ ከበሮ እየደለቅን፣
በቁስል ላይ ብረት አግለን የሰደድን፣
ወዮልን! ወዮልን! ጊዜአችን ሲጠራን፣
ከመቃብር ከቶ ቅጣቱን ሊሰጠን።

አቃቤ-ሕግ ዳኛ ሸማግሌ ሆነን፣
ፍርድን ስንገመድል ስንጠመዝዝ የኖርን!
ፍትህን በጫማ ደጋግመን የረገጥን፣
ወዮልን! ወዮልን! መሬት ስታሰምጠን፣
ሽቅብ ቁልቁል አይታ ፍርድ ስትሰጠን።

ስስትና  ጉጉት ተቆልለውብን፣
ክፋት ምቀኝነት ተከምረውብን፣
የዘር ልክፍት ቆሌ ጎጆውን ሰርቶብን፣
ወዮልን! ወዮልን! መሬት ስትጎትተን፣
ጭነታችን ከብዶ ወደ ታች ሲያሰምጠን።

እውነትን ተናግረን ማረግ እምቢ ብለን፣
ውሸትን ለፍልፈን መውደቅን የመረጥን፣
ወዮልን! ወዮልን! መሬት ስትውጥን፣
በነፍሳችን ቋጥራ ዝቅዝቅ ስትደፍቀን።

በጥቅም መርዝ ነፍዘን ማስተዋል ያቃተን፣
ቅዠቱን ራዕይ ቅጥቃጤን ህልም እያልን፣
ማፍረስን ግንባታ ጥፋትን ልማት ብለን፣
በሰባራ መርከብ መንሳፈፍ ላይ ያለን
አይነ-ስውር ነጂ  ካርቶን ኮምፓስ አምነን፣
ወዮልን ወዮልን ማእበል ሲመታን፣
ጥቡልቅ ጥቡልቅ ስንል እየተንጠባጠብን፣
ነፍሳችን ስትወጣ አረፋ እየደፈቅን።

እጅና እግራችንን በሐጥያት ዘፍዝፈን፣
ሰይጣን አዳራሽ ውስጥ ሰተት ብለን ገብተን፣
ለፈራሽ ሥጋችን ሳስተን ተንሰፍስፈን፣
ህሊና እንደ ቅርፊት ግሽልጥ አርገን የጣልን፣
ውዮልን! ወዮልን! መሬት ስትፈርድብን፣
ወደ ታች አስምጣ መልሳ ስተፋን፣
ትውልድ ለዘላለም አጥብቆ እንዲረግመን፣
ዳግምም  ሰልቅጣ  ዝቅዝቅ ስትደፊቀን፣
ናዳ እየለቀቀች ዝንተ-ዓለም  ልትወግረን።

ወዮልን! ወዮልን! ወዮልን! ወዮልን!

በላይነህ አባተ(abatebelai@yahoo.com)
ጥር ሁለት ሺ ሰባት ዓ.ም.